# ፓለቲካዊ ቁዘማና ገለልተኝነት በስዊዝ ቅንጅት

የዚህ ጽሁፍ አላማ በቅንጅት ምስቅልቅል ዙሪያ በላዕላይ መዋቅሩ አካባቢ ስለሚስተዋለው የፓለቲካ ምስቅልቅል political crisis ሀሳብ ለመስጠት ሳይሆን ጸሃፊው አባል በሆነበት የስዊትዘርላንድ የቅንጅት ድጋፍ ሰጪ ምዕራፍ ወቅታዊውን የንቅናቄውን እውከት በተመለከተ በሚስተዋሉ አስተሳሰቦችና ተግባራት ላይ ውይይትና ክርክር ለመክፈት የዝምታውን በረዶ ለመስበር በማለም ነው፡፡የቅንጅት ስዊትዘርላንድ የድጋፍ ምዕራፍ በወቅታዊው የቅንጅት ምስቅልቅል ዙሪያ የካንቶን ተወካዮችን ም|ቤትን አልያም ልዩ አጠቃላይ የአባላት ጉባኤን አካሂዶ አቋም ባይዝም የዚህ ጽሁፍ መነሻ በአመራር አባላቱ አካባቢና በተለይም በፓልቶክ መድረኩ ላይ በተደጋጋሚ በተገለጹት ያልጸደቁ የድርጅቱ አቋሞችና ተግባራት ላይ በመንተራስ ነው፡፡

የቅንጅት ስዊትዘርላንድ የድጋፍ ድርጅት በዚህ ወቅት ከሚታይበት ደካማ አሰራር ውስጥ ዋንኛው ለመመስረቱ መሰረት የሆነው ዲሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ በታወከበት ባለንበት ጊዜ የድጋፍ ድርጅቱ የመረጠው ቁዘማ ነው፡፡ በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ድርጅቱ ኮማ ውስጥ አልያም ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ውስጥ የገባም ይመስላል፡፡ የድጋፍ ድርጅቱ ስራ አምራርም ይሁን አባላት መደበኛ የወቅታዊ ሁኔታ ግምገማና የተግባር ንድፍ አልወሰኑም ፡፡ ይህ ጽሁፍ በሚዘጋጅበት ወቅት በሀገር ውስጥም ይሁን በውጭ ሀገር ያሉ ሚሊዮኖች የቅንጅት ደጋፊዎች እጅግ መንፈስን በሚሰብር የፓለቲካ ሁኔታ ውስጥ ሆነውም ቢሆን ቅንጅት ዳግም ልደቱን አድሶ ወደ ነጻነት መንገድ ይመራናል ብለው ተስፋ ያደርጋሉ፡፡ በተለይ በውጭ ሀገር ያለነው የድርጅቱ ደጋፊዎች ከወያኔ የቀጥታ በትር አድማስ ውጭ እንደመሆናችን ቁጭታችን ቁጭት ብቻ ሆኖ እንዳይቀር አቅም የፈቀደውን ሁሉ ለማድረግ ሀገር ቤት ካሉት ኢትዮጵያውያን የተሻለ እድል በአንዳንድ አንጻር እንዳለን ይታመናል፡፡ ትርጉም ያለው የፓለቲካ ተሳትፎ እንድናደርግ ደግሞ የድጋፍ ድርጅቶች በተሰደድንባቸው ሀገራት ሁሉ መስርተናል፡፡ በመሆኑም ህዝባዊው እንቅስቃሴ ከወያኔም ይሁን ከውስጥ ምግባረ ብልሹዎች ጥቃት ሲሰነዘርበት ሰብሰብ ብለን ምን እንድርግ ልንል ይገባል፡፡ የቅንጅት ስዊትዘርላንድ የድጋፍ ድርጅት በዚህ የፓለቲካ ምስቅልቅል ወቅት የድጋፍ ድርጅቱ አንቀሳቃሽ ህዋስ የሆኑት የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴውም ይሁን የካንቶን ተወካዮች ም| ቤት ምንም አይነት የውይይት መድረኮች አልፈጠሩም፡፡ድርጅትና መሪ የሚያስፈልገን ከሁሉም ከሁሉም ቀውጢውን ወቅት እንዲያሻግሩን መሆኑ ተዘንግቶ አባላት በጉዳዮች ላይ የጋራ

ግንዛቤ እንዲፈጥሩ ያንንም መሰረት አድርገው አዎንታዊ የፖለቲካ ተግባራት ላይ እንዲሰማሩ ምንም ጥረት አልተደረገም፡፡ አንድ የፖለቲካ ስብስብ ፖለቲካዊ ተግባራትን ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታዎችን እለት በ እለት እየተከታተለ ካላከናወነ ምን ይሆን ፋይዳው ?

የቅንጅት ስዊትዘርላንድ መሪዎች በግልጽ እንደሚረዱት ዛሬ በነጻነቱ እንቅስቃሴ ላይ ቢያንስ ቢያንስ ከሶስት አቅጣጫዎች የጠነከሩ ጥቃቶች እየተሰነዘሩ ይገኛል ፡፡ ወያኔ ቀድሞውንም ዲሞክራሲያዊ ሀይሎችን ከማደን ወደ ኋላ ስለማይል የዚህኛው ወገን ጥቃት እጅግም አይደንቅ ይሆናል፡፡ ሌላው አስገራሚው የህዝባዊው እንቅስቃሴ ደመኛ ደግሞ የኢህአፓ አክራሪ ክንፍ ነው ፡፡ ይህ ክንፍ ፖለቲካን ተደጋግሞ እንደሚመሰረት የቼዝ ጨዋታ የሚቆጥር በማካቬያላዊ ተንኮል የተካነ በሀሳብ ለተለዩው ለየትኛውም ወገን የትኛውንም የጥፋት መንገድ ከመጠቀም የማይመለስ ራዕይ አልባ ስብስብ ነው፡፡ ሶስተኛው ወገን እቅንጅት ውስጥ ሊያድግ የሚድህው አምባገነንነት ነው ፡፡ በቅርቡም ሪፖርተር የተሰኘው የወያኔ ልሳን ኢንጂነር ሀይሉ ሻውልን የሀገር ሉአላዊነት ጠበቃ አድርጎ በርዕሰ አንቀጹ አትቷል፡፡ አክራሪው የኢህአፓ ክንፍ ታይቶ በማይታወቅ ፖለቲካዊ መተጣጠፍ በሌላ የፖለቲካ ድርጅት የውስጥ ጉዳይ ገብቶ ከመሪያችን ቆራጥ አመራር ወዲያ እያለ መፈክር ሲሰብቅም እየተስተዋለ ነው ፡፡ ዋናው የነጻነት ጠሮች ደመኛ ዲሞክራሲያዊው እንቅስቃሴ ስለሆነ ይሄ የሶስትዮሽ ርብርብ ብዙም አይገርም ይሆናል፡፡ የዲሞክራሲው ንቅናቄ እስንግ ገብቶ ባለበት በዚህ ወቅት የድጋፍ ድርጅቶች ይህን መሰሉን የአጥፊዎች ርብርብ ለአባላት ግልጽ አድርገው ጠንካራ ንቅናቄ ካልወጠኑ እምኑ ላይ ይሆን ፋይዳቸው ? ወይንስ ጉዳዩ ፈር ከያዘ በሁዋላ እንዲህ አቅደን እንዲያ አድርገን ነበር ማለቱ ነው የሚሻለው ?

ተደጋግመው ከተገለጹት የድርጅቱ አቋሞች አንዱ ገለልተኛነት ነው፡፡ በአጭር ቃል አሁን ባለው የቅንጅት ሀይል አሰላለፍ የየትኛውም ቡድንን አስተያየቶችና ተግባራት አንደግፍም ለማለት የተፈለገ ይመስላል ፡፡ ትልቁ የዚህ አመለካከት ጤና ማጣት የመነጨው ይህንን የገለልተኝነት መመሪያ እንዴት ባለ የድጋፍ ድርጅቱ የስራ አካሄድ ተደረሰ የሚለው ላይ ነው፡፡ የድጋፍ ድርጅቱ በቅንጅት ወቅታዊ ምስቅልቅል ላይ በየትኛውም የምዕራፉ የሃላፊነት እርከኖች ውይይት አላካሄደም፡፡ እንዲያ ከሆነ የትኛውም የገለልተኝነት እንበለው የቡድንተኝነት አቋም በማንኛውም የድጋፍ ድርጅቱ አመራር አባል ይሁን እንደ ፓልቶክና ድረ ገጽ በመሳሰሉት የድርጅቱ ልሳናት ይገለጹ ከግለሰብ አቋምነት የዘለለ ፋይዳ የላቸውም፡፡

ይህንን የገለልተኝነት አቋም በቅንጅት ዙሪያ ካሰባሰቡን የፓለቲካ ሃሳቦች አኳያ ሲመረመር ደግሞ የአቋሙን ብላሽነት በቅጡ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በስደት በየክፍለ አለማቱ ያሉ ኢትዮጵያውያን በየአካባቢያቸው ወዳሉት የድጋፍ ድርጅቶች የተሰባሰቡት በ እነዚህ ምዕራፎች ባሉት የአመራር አባላትና ደጋፊዎች ተክለ ሰውነት ዙሪያ ከመሆን ይልቅ ወቅታዊው የነጻነት እንቅስቃሴ ባነገበው የሃሳብ ጥራትና ይህንንም ሀሳብ እተግባር ሊያደርሱ በተሰለፉት የህዝብ ልጆች ዙሪያ ነው፡፡ በህዝባዊው እንቅስቃሴ የስራ አመራር ዙሪያ ያሉት ወገኖች በአንዱ ወይም በሌላው ምክንያት ከአቋማቸውና ከእውነቱ ባፈገፈጉ ቁጥር ህዝብም የነጸነት መንፈስ አብሮ ሽብረክ አይልም፡ ፡ የቅርብ ጊዜው የቅንጅት ታሪክ ያሳየንም ይህንኑ ነው፡፡ ህዝብ አቶ ልደቱ አያሌው ለትግሉ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ጠንቅቆ ያውቅ ነበር ነግር ግን የግለሰቡ አቋም ወያኔ ወያኔ ሲሸት የእርሳቸው አፍንጫ ተደፍኖ ይሆናል እንጂ የህዝብ የስሜት ህዋሳት ሁልጊዜም ህያው ናቸውና እውነቱን ለመረዳት ምንም አይነት ፕሮፓጋንዳ አላስፈለገም፡ ፡ ግለሰቡ በማወቅ ስሜት ተነድተው ራሳቸውን በተገኙት መንገዶች አጋልጠዋልና፡፡ የህዝብን የነጻነት እንቅስቃሴ ትላንትም ዛሬም እንዲሁም ነገም ሊበትኑ የሚነሱ ወገኖች ከየትኛውም ወገን ቢነሱ እንደ ኮሚኒስታዊው ዘመን በካውንተር ፕሮፓጋንዳ ገንዘብና ጊዜ ማጥፋት አያስፈልግም ፡፡ ምክንያቱም የኢትዮጵያ ህዝብ የትኛው የቁሳር የትኛው የእውነት እንደሆን ለመረዳት ብዙም አያዳግተውም ለምን ቢባል የህዝብ ንቅናቄ ሊትመስ ፔፐር የነጻነቱ እንቅስቃሴ ገዥ ሃሳቦች ብቻ ናቸውና፡፡ የተሰባሰብነው ግልጽ በሆኑ መርሆዎች ዙሪያ ከሆነ የድርጅት መሪዎች በንዋይ እንበል በማህበራዊ ትስስር እሙስና ዙፋን ላይ ፊጥ ቢሉ እጅግም ሲከፋ የወያኔን አገዛዝ በእምቢልታና በበገና እናጅበው ቢሉ እነርሱው ግራ ይጋቡ ይሆናል እንጂ በዚህ ዘመን ግራ የሚጋባም ለአፍታም ደንገር የሚለው ከቶውንም አይገኝም፡፡

በዚህ ዘመነ የፍየል ወጠጤ የትግሉ አስተባባሪዎች በሃሳብና ተግባር ልዩነት ሲታዩባቸው የመለስን ግድያ በአለም አደባባይ ያወገዘው ኢትዮጵያዊ ፣ የልደቱን ክህደት ወግድ ያለ የድጋፍ ድርጅት፣ ዛሬ የአምባገነንትና የሴራ ፓለቲካ መልኩን ቀይሮ ህዝባዊው እንቅስቃሴ ውስጥ ለማደግ ሲውተረተር እንደ ወትሮው ከጅምሩ ሊቀጨው እጅ ለእጅ ተያይዞ ከሜልቦርን እስከ ሲያትል ከጆሃንስበርግ እስከ ኦስሎ ይረባረባል እንጂ ዝም እንበል እንተኛ አይናችንን እንጨፍን ጆሮአችንን እንክደን አይልም፡፡ እውነትና ሀሰት ጥርት ብለው እየታዩ የለም ገለልተኛ ነን የተሰኘ ፓለቲካ ፖለቲካዊ ቲያትር ብቻ ነው ሊባል የሚገባው ፡፡መለስ ሲቀጥፍ አባይ ቀጣፊ ብለነዋል

ለአለምም እርቃኑን እንዲታይ አድርገናል፡፡ መለስ መሪዎችን በዘር ማጥፋትና ምድር ልትፈጥረው በምትችለው ወንጀል ሁሉ ሲከስ በጄ እንዳላልነው ኢንጅነር ሃይሉ ሻውልም የትግል አጋሮቻቸውን መሰረት በሌላቸው ክሶች ሲተበትቡ ህሊናችን በጄ አይልም፡፡ ወቅታዊው ትግል በሁለት ወገን እንደተሳለ ሰይፍ ነውና እቅንጅት ውስጥም አምባገንነትና ምግባረ ብልሹነት ስሩን ሊተክል መሬት ሲሰረስር ገለልተኛ እንሁን ብሎ አቓም አረሙ እንዳይጨፈለቅ አጥር እንጠርለት እንከልለው እንንከባከበው ማለት እንደሆነ ለመረዳት የኒውክለር ሳይንስ አይሆንብንም፡፡

ይህንን እንዳላዩ ሆኖ ዝም ማለትን አጉል ገለልተኛነትን እውቁ የሰብአዊ መብት ታጋይ ማርቲን ሉተር ኪንግ አሜሪካ ቬትናምን በወረረች ወቅት በስመ ብሄራዊ አርበኝነት ዝምታን ለመረጡ ወገኞች በሚከተለው መልኩ ተችቶታል፡፡ "A time comes when silence is betrayal." በእኛም የቅንጅት ወቅታዊ ጉዳይ ላይ ዝም እንበል ገለል እንበል ማለት የህዝብን እንቅስቃሴ እንክዳ ከማለት ሌላ ምንም ሊባል አይችልም፡፡ ስለሆነም የድርጅቱ አቓም ገለልተኝነት ነው ከተባለ የድጋፍ ድርጅቱ የአመራር እርከኖች ግልጽ ውይይቶች ተካሂደባቸው አባላትም በአስተውሎታቸው ላይ ተንተርሰው የሚደርሱበት የምስቅልቅል crisis ጊዜ የተግባር መመሪያ ሊወጣለት ለዚህም በድርጅቱ ተከታታይ ተግባራት ላይ በገቢር የሚታይ ሊሆን ይገባል ፡፡

ሌላው አነጋጋሪ የቅንጅት ስዊትዘርላንድ የድጋፍ ድርጅት የገለልተኛነት አቓም ይህው ገለልተኝነት ሀቀኝነት የጎደለው መሆኑ ላይ ነው፡፡ በወቅታዊው የቅንጅት ምስቅልቅል ዙሪያ የታህሳሱን አምባገነንነት የሚደግፉ ወገኖች በስም ማጥፋትና አሉ በሚባሉት ቆሻሻ የፓለቲካ ስልቶች ሁሉ የህዝብን እንቅስቃሴ በጽናት ለማስተባበር እየጣሩ ያሉትን መሪዎች ሊጠልፉ የህዝብንም እንቅስቃሴ አቅጣጫ ሊያስቱ የአቅማቸውን እየሞከሩ ነው ፡፡ ይህ አምባገነን ቡድን በተለይም በውጭ ሀገር እዚህ ግባ የሚባል የድጋፍ ሀይል የሌለው ሲሆን ህዝብ ማንነቱን ይበልጥ በተረዳ ቁጥር ኢህአፓን ከመሳሰሉ የትግል መጨረሻ የፓለቲካ ቡድንን ከማምለክ እልፍ የማይል አላማ ክሌላቸው ፓርቲዎች ጭምር ደጋፊ እየተዋሰ ከዚያም ሲያልፍ የሴራ ፓለቲካውን ንድፍ ሁሉ እዚያው እያስነደፈ መሬት ላይ በተጨባጭ ደጋፊ መቁጠር ቢያቅተው በአሁኑ ወቅት ህዝብ አንቅሮ እተፋቸው ሬዲዮኖችና የፓልቶክ መድረኮች ላይ ተንጠልጥሎ ይገኛል ፡፡

የዚህ ቡድንን ሃሳቦች ወደ ህዝብ ለማስረጽ የተለያዩ ካድሬዎቹ በተለያየ ጊዜያት የስዊዝ ቅንጅትን የፓልቶክ መድረክ እንዲጎበኙ ሁኔታዎች ሲመቻቹላቸው ቆይቶአል፡፡ ሁላችን እንደምናውቀው በፓለቲካ ፓርቲዎች ስር የሚደራጁ የመገናኛ ብዙሃን ዋንኛ ተግባር የድርጅቱን አላማዎች ለአባላትና ደጋፊዎች ማስተዋወቅ ማስተማርና ዘላቂ የሆኑ የፓለቲካ ሃሳቦች እንዲሰርጹ ማድረግ ነው ፡፡ በግልጽ ምሳሌ ወያኔ በድምጺ ወያኔ በተሰኘው ሬድዮው የቅንጅት የፓለቲካ ሃሳቦችን በየትኛውም መንገድ አያስተላልፉም፡፡ የፓለቲካ ፓርቲዎች የመገናኛ ብዙኋን - ፓርቲ ልሳናት ዋንኛ አላማ ወጥነት ባላቸውና በታለሙ አላማዎች ተከታታይ የሃሳብ ግንባታዎችን ማካሄድ ነው፡፡ ከዚህ የተለመደ አሰራር አኳያ  ስንመለከተው የቅንጅት ስዊትዘርላንድ ፓልቶክ  ኢ-ገለልተኛ ብቻ ሳይሆን ወገንተኛ የፕሮፓጋንዳ ተግባር ሲያካሂድ ቆይቶዋል፡፡ በቅርቡ በመወያያ መድረኩ ላይ ያስተዋልነው ጉዳይ ለዚህ አንድ ምሳሌ ነው፡፡ ዲያስፓራ በሚባለው የመወያያ መድረክ በቅርቡ የአቶ ሀይሉ ሻውልን ህገ ወጥ እርምጃ የሚደግፉ ወገኖች ርምጃው እንዲያውም ዘገየ ባሉበት መድረክ አንድ ግለሰብ ከኒውዮርክ ተወክለው የአቶ ሀይሉ ሻውልን እርምጃ ሲያንቆለጳጵሱ በተደመጠ ማግስት በስዊዝ ቅንጅት የመወያያ መድረክ ላይ ገለልተኛ ተሰኝተው ይቀርቡና በህዝባዊው እንቅስቃሴ ሁነኛ ሚና ሲጫወቱ    የነበሩ ግለሰቦችን መሰረት በሌላቸው ክሶች ሲከሱና ፍርድም ሲስጡ ያመሻሉ ፡፡ እንግዳው ካቀረቡት ዲስኩር እንግዲህ የዝግጅቱ አስተባባሪዎች ምን አይነት ሀሳብ ሊገፉ ነው እንግዳውን የጋበዙት ብለን አድማጮች እንገምት ? ገለልተኝነትን ?  ፈጽሞ ፡፡ ለእንደዚህ አይነት ግዙፍ ስህተቶች በተደጋጋሚ የሚሰጡት ምክንያቶች የጊዜ ጥበትና አባላት የተለያዩ እንግዶችን በመጋበዝ የሚያደርጉት ተሳትፎ አናሳነትን ነው ፡፡ ምን ጊዜ ቢያንስ ምን እንቅልፉም ደጋፊዎች ብንበዛ ሀገራዊ ዜማዎች በፓልቶክ ፎረሙ ቢተላለፉ ይሻላል እንጂ ከፋፋይና የህዝብ ወገኖችን የሚያዋርዱ ቃለ መጠይቆች በፍጹም ምንም አይነት ገንቢ አላማ ሊሰየምላቸው አይቻልም ፡፡

የቅንጅት ስዊትዘርላንድ ድጋፍ ድርጅት በወቅታዊው የፓርቲው ጉዳዮች ላይ የድርጅቱን መርሆዎች የተንተራሰ ጠንካራ አቋም ይያዝ የሚል ጥያቄ ጉዳዩን የሚያነሱት አባላት የገለልተኝነት ጽንሰ ሃሳብ ስላልገባቸው አልያም የፓለቲካው ጡዘት አዕምሮአቸውን የሚያስት ስሜታዊነት ውስጥ ከቶአቸው አይደለም፡፡ ቢያንስ ቢያንስ ከትውስታ ማዕቀፍ ርቆ ያልሄደው የቅንጅት አለም አቀፍ ተሞክሮ ዛሬ መደገም እንደሌለበት ግልጽ ሰለሚሆንም ነው፡፡ ቅንጅት አለም አቀፍ ችግሩ ወደ አደባባይ

ከመውጣቱ ቀደም ብሎም ብዙ አሉባልታዎች በአመራሩ አባላት መሀከል ያለውን የአሰራር ልዩነት መሰረት አድርገው ይናፈሱ ነበር፡፡ ሊቀመንበሩ ሻለቃ ዮሴፍ ያዘው ሁለቱን የአመራር አባላት በወያኔነት ከሰው የእግድ ውሳኔ ሲያስተላልፉና ድርጅቱም ለሁለት ሲከፈል ቅንጅት ስዊትዘርላንድ የገለልተኝነትን አቋም እከተላለሁ ሲል በአመራሩ በኩል ለአባላቱ አስታወቀ፡፡ በወቅቱ ይህንን ገለልተኝነት ያሉትን አቋም የወሰዱ በመላው አለም የሚገኙ ግለሰቦችና የድጋፍ ድርጅቶች ይህ አቋማቸው ምንም ያህል ምክንያታዊ በሆኑ አመለካከቶች ላይ የተመሰረተ ቢሆን ከዚህ አቋም አጥፊዎች ምን እንዳመረቱበት ቢያንስ ቢያንስ ዛሬ ሳይረዱት አይቀርም፡፡ በአጭር ቃል ቅንጅት ስዊትዘርላንድም ይሁን ሌሎች የገለልተኝነት አቋም የዘመሩ የድጋፍ ድርጅቶች የሻለቃ ዮሴፍ የኦክቶበር ጉንፋን ቃሊቲ ድረስ ዘልቆ ሚኖሶታ ላይ ለታወጀው የታህሳሱ አምባገነንነት የመፈልፈያ ጊዜ እንደሰጡ እንደሚገለጽላቸው እሙን ነው፡፡ በመላው አለም የሚገኙ የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶችና አባላት በሻለቃ ዮሴፍ ቡድን የተወሰዱትን ህገ ወጥ ተግባራት ከህገ ደንብም ይሁን ከመርሆዎች አኳያ ተንትነው የማያወላዳ አቋም ይዘው ቢሆን ኖሮ ዛሬ ኢንጂነየር ሀይሉ ሻውል የህዝብን መስመር ትተው የራሳቸውን መንገድ ባልጀመሩ ነበር፡፡ ስለሆነም የድጋፍ ድርጅታችን ትላንት ከፈጸመው ስህተት ሊማርበት የሚችልበት ዕድል ከማዕዱ ስላለ በስመ ገለልተኝነት አምባገነኖችና የፓለቲካ ቧልተኞች የህዝብን እንቅስቃሴ መስመር እንዳያስቱ በሚገባና ግልጽ በሆነ ቋንቋ በቃ ሊላቸው ይገባል፡፡ ስለሆነም ያሳለፍናቸው የፓለቲካ እንቅስቃሴ ተሞክሮዎችም የአጉል ገለልተኛነት አቋምን እርባና ቢስነት በገቢር ስላስተማሩን በክብ ጠረጴዛ አባላትን ጥልቅ የሆነ የሁኔታዎች ምርመራ Situational Analysis አድርጎ የጸና አቋም ላይ መድረስ ለነገ የሚባል ተግባር እንዳልሆነ ለስዊትዘርላንድ ቅንጅት የድጋፍ ድርጅት የአመራር አካላትም ይሁን ለአባላት አትኩሮት ማቅረቡ የሚመከር ተግባር ነው፡፡

ለማጠቃለል ሁላችንን ወደ አንድ መድረክ ያሰባሰብን ቅንጅት አደጋ እንደተቃጠበት እጅግም የማያከራክር እውነታ ነው፡፡ ህወሃትም ይሁኑ ሌሎች አምባገነን ሀይሎች ህዝብ ግራ ቢጋባ ፣ ምን ቸገረኝ ብሎ ከሀገራዊ ፓለቲካ ቢያገል፣ በውስጠ ፓርቲ ፓለቲካ እንካሰላንቲያ ተወጥሮ አይኑን ከእነርሱ ጥፋት ላይ ቢያነሳ ደስታቸው ልክ ያጣል እንዲያውም ለጣያቶቻቸው ግብር ባይገብሩ ነው? የህወሃትስ ትልቁ የፓለቲካ ስልት ተከራክሮና ተሟግቶ ሀሳብን ከመሸጥ ይልቅ ህሊናን በዘር፣ በሙስናና ሌሎች ተዛማጅ ማዘናጊያዎች መሸበብ አይደለምን ? ስለሆነም የድጋፍ ድርጅታችን ህያው የሆነ የፓለቲካ ተቋም ይሆን ዘንድ እውነትና ሀሰት እፍርድ ወንበር ላይ በተቀመጡ ጊዜ

የትኛውንም ካባ ይደርቡ እውነቱን እውነት ሀሰቱን ሀሰት ይበል እንዲያ ሲሆን የተሰበሰብንበት አላማ ጊዜ የማይሽረው ለሀገራችንም ትንሳኤ መሰረት ይሆናል ፡፡

እግዚያብሄር ኢትዮጵያን ይባርክ

ሳምሶን ብርሀኑ samsonbrh@gmail.com
ዴሴምበር 24 .2007